

፭፪. ባሕታዊ አባ ሚሳኤል

(ABBA MISAEL THE HERMIT)

የኤል ቃላሞን ገዳም አበምኔት አባ ይስሐቅ ይህን ታሪክ ነገረን፦

"አንድ ቀን እለዉድ ጠዋት በገዳሙ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባለሁበት "አባ ይስሐቅ፣ እባክህ ከልጆችህ እንደ አንዱ አድርገህ ተቀበለኝና የምንኩስና ልብስ አልብሰኝ ይህን የማድረግ ስልጣን እንዳለህ አውቃለሁና፣ ምክንያቱም መነከሳቱ ለአንተ ምን ያህል እንደሚታዘዙልህ አይቻለሁ" ያለኝን የአንድ ወጣት ድምፅ ከወደ ኋላዬ ሰማሁ። ዞር ስል ከፊቴ አንድ እድሜው ዐሥራ ሁለት ዓመት የሞላው ወንድ ልጅ ቁሟል፣ ግን ብዙ መንፈሳዊ ፍሬዎችን እንዳፈራና የአምልኮ ሕይወትን በሙሉ ልቡ ፈልጎ እንደመጣ ተሰማኝ። ከዚያም "ልጄ፣ ሒድና ገዳሙ ውስጥ ካሉት በኣቶች በአንዱ ውስጥ ለትንሽ ጊዜ ቆይ፣ ፈተናዎችንና ሥጋዊ ፍላጎቶችህን በብሕትውናና በማያቋርጥ ጸሎት በድል ለመወጣት ትእግስተኛ እና ጠንካራ ከሆንህ መነኩሴ መሆን ትችላለህ" አልሁት። በተጨማሪም ቅዱሳት መጻሕፍትንና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

መጻሕፍትን እንዲያጠና እንዲሁም ሁሉንም መዝሙራት በቃሉ እንዲይዝ መክርሁት። ከገዳሙ መነኰሳት መካከል አንዱን ጠራሁና ከልጁ ጎን ሆኖ የምንኩስናን ሥርዐት ና ባህል እንዲያስተምረው ጠየቅሁት።

ለዚህ ታዳጊ ልጅ በጣም አስብ ስለነበር "ልጄ፣ አሁንም በጣም ልጅ ነህ፤ ምናልባት ለወላጆችህ አልታዘዝም ብለህ ወደዚህ አምልጠህም ሊሆን ይችላል። እባክህ ስለአንተ እውነቱን ንገረኝ" ብዬ ጠየቅሁት።

"ወላጆቼ በጣም ክፉዎች ነበሩ፤ በፍጹም ጸልየው የማያውቁና ለሌሎችም ምንም ዐይነት ፍቅር የሌላቸው ነበሩ። በእድሜያቸው በጣም ሸምግለው ስለነበርና ልጅ መውለድ ባለመቻላቸው ምክንያት በጣም አዝነው ይኖሩ ነበር። በመጨረሻም ያሉበትን ሁኔታ ለአንድ መነኩሴ ካህን ይነግሩታል፤ እርሱም "በመጀመሪያ ሂዳችሁ ንስሓ መግባት ይኖርባችኋል፤ ከዚያም እግዚአብሔር ወንድ ልጅ ይሰጣችኋል" አላቸው። በዚያች ቅጽበት ንስሓ ገብተው በትጋት ጸለዩ፤ ድሆችንም አጽናኑ። በመቀጠልም እንዴት መጸለይ እንዳለባቸው እንዲያስተምራቸው በመንደራቸው ያለን አንድ ካህን ጠየቁ፤ እርሱም "አቤቱ እንደ ቸርነትህ መጠን ማረኝ፤ እንደ ምህረትህም ብዛት መተላለፌን ደምስስ። ..." /መዝ 50/ የሚለውን የዳዊትን መዝሙር እንዲያስታውሱ ነገራቸው። በመጨረሻም እግዚአብሔር ልጅ ሰጣቸው። እነርሱም እግዚአብሔርን በመፍራትና በፍቅር አሳደጉኝ። ወላጆቼ ብዙ ላሞች፣ ፍየሎች፣ የቤት እቃዎች እና ሌሎችም እጅግ ብዙ ሀብት ነበራቸው፤ ሁሉንም ሀብታቸውን ለድሆች ሰጡ።

የዐምስት ዓመት ሕጻን እያለሁ አባቴ ሞተ፤ ከአንድ ዓመት በኋላ ደግሞ እናቴ ተከተለችው፤ ስለሆነም እኔ ብቻዬን ቀረሁ። አንድ ቀን ለራሴ "አሁን አባቴ የት ነው? እናቴስ የት ነው ያለች? ከእነርሱ በፊት

የሞቱ ሰዎችስ የት ነው ያሉት?" እያልሁ እያሰብሁ ነበር። በዚህ ምድር ላይ ያለው ይህ ዓለም ለዘለዓለም እንደማይቀጥል ተገነዘብሁ፤ ስለዚህም ከዓለም ወጥቼ ወደ ምድረ በዳ ማምለጥ እንዳለብኝ ወሰንሁ። ..."

ይህ ልጅ ወደ ገዳሙ ከመጣ ገና አንድ ዓመት እንኳን ሳይሞላው ሁሉንም የቤተ ክርስቲያን ዶግማና ቀኖና ተማረ፤ ሁሉንም መንፈሳዊያት መጻሕፍት በቃሉ አጠና፤ በከፍተኛ ትጋትም ይጾምና ይጸልይ ነበር። እንዲጠብቀውና እንዲንከባከበው የሰጠሁት አባት አንድ ቀን ወደ እኔ መጣና "አባ፣ በእርግጥ ይህ ልጅ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች የተሞላ ነው" አለኝ።

እኔም ይህ ልጅ ሁሉንም ፈተናዎቹን በትእግስት እንዳለፋቸው በተሰማኝ ጊዜ እና ከልብ የሆኑ ጸሎቶቹን ባየሁ ጊዜ የምንኩስና ልብስ አልብሼ ስሙንም ሚሳኤል ብዬ ሰየምሁት፤ በዚያች ቅጽበት በመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ብርሃን ፊቱ እንደ ፀሓይ አበራ።

እርሱም መኖሩን እንኳን የሚያውቅ ሰው እስኪጠፋ ድረስ በዘኣቱ ውስጥ በብሕትውና ኖረ። ከዚያም አንድ ቀን ሌሊት ከመነኰሳት አንዱ ወደ እኔ መጣና "አባ፣ 'ነፍሴ ሆይ፣ የሰው ሥጋ ሁልጊዜ የዓለም የሆነውን እንደሚመኝ ዕወቂ፤ ይህም የኃጢአት ውጤት ነው፤ ስለዚህ ለመዳን ከፈለግሽ ከኃጢአት አምልጭ' እያለ ራሱን የሚወቅስ የሰው ድምፅ ሰማሁ" አለኝ። እኔ ደካማው ይስሐቅም ዲያብሎስ ውጥኑን መነኩሴ በዓለማዊ ጥቅሞች እያባበለው እንደሆነ ተረዳሁ። ...

ስለሆነም አባ ሚሳኤልን ላየው ሔድኹ። ወደ በኣቱ ስቃረብ የመንፈቀ ሌሊት ጸሎቱን ገና አልጨረሰም ነበር፤ ስለዚህ እስኪጨርስ ድረስ ከውጭ ቆየሁ። ከዚያም ወደ በኣቱ በመልካም አቀባበል አስገባኝ፣

እኔም "ተወዳጁ ልጄ ሆይ፣ በዚህ ሌሊት የተፈጠረ ነገር አለ? ጠላት ዲያብሎስ ረበሸህን?" ብዬ ስጠይቀው በፊቱ ተንበርክኮ "አባ፣ ዲያብሎስ እኔ ያለሁበትን ሁኔታ ያውቃል፣ ግን ጸሎቶቼን መስማትን መቋቋም አይችልም" አለኝ። እኔም ከሰሎሞን መጽሐፍ ያነበብ እንደነበር ተገነዘብሁ፣ ሚሳኤልም ከብልሆችና ጥበበኞች አንዱ መሆኑን አረጋገጥሁ።

አንድ ቀን ልጎበኘው ወደ በኣቱ ሐዲሽ፣ ከበኣቱ በር አጠገብ በቀምሁ ጊዜ "ረዳት ሁነኝ፣ አትጣለኝም፣ የመድኃኒቱ አምላክ ሆይ አትተወኝ። አባቴና እናቴ ትተውኛልና እግዚአብሔር ግን ተቀበለኝ" /መዝ 27/ እያለ ሲጸልይ አገኘሁት። የበኣቱን በር ሳንኳኳ በሩን ከፍቶ በደስታ ተቀበለኝ። ሰውነቱን ወደ ገዳም ሲገባ እንደነበረው ሆኖ ሳይሆን እንደ ደረቀ እንጨት ሆኖ አገኘሁት። እጆቹና እግሮቹ እንደ ቱምር ግንድ ቀጭጨዋል፣ በልዩ ፍቅርና ደግነት ወደ እኔ ትኩር ብሎ ከሚያይባቸው ብሩህ ዐይኖቹ ውጭ ከሰውነቱ ምንም የቀረ ነገር ያለ አይመስልም፣ አልቋል። "አባ፣ ደስ ሊልህና ሀሴትን ልታደርግ ይገባሃል" አለኝ። እኔም እያለቀስሁ "እንዴት ልደሰት እችላለሁ? ወደዚህ ገዳም ስትገባ ውብና ጤናማ ልጅ ነበርህ፣ አሁን ግን ተመልከት፡- እንደ ሞቱት ሆነሃል!" በማለት መለስሁለት። ሚሳኤልም በፍቅር እንዲህ በማለት መለሰልኝ፡- "በእነዚህ ዓመታት ውስጥ እግዚአብሔር ዐይኖቼን አላፈዘዛቸውም፣ ይልቁንም ለጸሎት መቀም እችል ዘንድ አበረታኝ እንጂ። ይህ ሥጋ ዓለምንና ዓለማዊ ፍላጎቶችን ይሻል፣ እኔ ግን ከዚህ እና እነዚህን ከሚመስሉ ነገሮች ከለከልሁት፣ በዚህ ምክንያት ሰውነቱ አሁን እንደምታየው ሆነ።" በፊቱ የቆመውን የዚህን የተባረከ ቅዱስ ታላቅነቱን እና የመንፈሳዊነቱን ከፍታ ተረዳሁ፣ ስለሆነም እንዲጸልይልኝ ጠየቅሁት።

...

ከዚህ በኋላ ደግነት በተሞላበት አተያይ ወደ እኔ ተመለከተና እንዲህ አለኝ፡- "አባ፣ ተኝቼ በሕልም ምን እንዳየሁ ልንገርህ? ከሦስት ቀን በኋላ ሰዎች ከአንተ መነኰሳት መካከል አንዱን መነኩሴ ፈልገው ከእስክንድርያ ደሴት ወደዚህ ገዳም ይመጣሉ። በንጉሡ የተላኩ ኃያላን ሰዎች ናቸውና በገዳሙ ላይ መከራን እንዳያመጡና መነኰሳትንም እንዳይገድሏቸው እንዳትከለክላቸው።" ከዚያም ሚሳኤል ግልቀስ ጀመረና "አባ፣ ሊወስዱኝ የሚገባ መነኩሴ እኔ ነኝ፣ ግን አባክህ እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ነውና አትዘን፣ እርሱ ጠባቂዬ ነው፣ ወደ አንተ ተመልሼ እንደምመጣ እርግጠኛ ሁን። በሚቀጥለው ዓመት በምድር ላይ ታላቅ መከራና መአት ይመጣል፣ ግን አትፍራ፣ እኔ ወደ አንተ እመጣለሁ፣ ከዚያም የእግዚአብሔር ፈቃድ ሲገለጥ ታያለህ" አለኝ። ሚሳኤል በነገረኝ ነገር በጣም ግራ ተጋብቼ ስለነበር ህልሙን አብረውኝ ለሚኖሩ መነኰሳት ወንድሞቼ አጋራኋቸው፣ እነርሱም በጣም ተገረሙ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ የቅዱስ ሚሳኤል ስም የተጻፈበትን ደብዳቤ ይዘው ሰዎች ከእስክንድርያ ወደብ ወደ ገዳሙ መጡ። በከፍተኛ ቁጣ ውስጥ ሆነው "ለሌላ ተጨማሪ ቀን በዚህ ቦታ እንዲቆይ አንፈቅድምና ይህን ሰው ወደ እኛ አምጡ" አሉ። እኔም በጣም ተጨንቄ ነበርና "ይህን መነኩሴ አላውቀውም፣ በዚህ ቦታ የለም" አልኋቸው። ወዲያውኑ በብረት ሰንሰለት ከእብነበረድ ምሰሶ ላይ አሰሩኝ። ሁሉንም መነኰሳት ከገዳሙ አስወጧቸው፣ እኔንም ወደ እስክንድርያ ሊወስዱኝ ፈልገው ነበር፣ አባ ሚሳኤል ድንገት በፊቴ ቆመና "ማንን ትፈልጋላችሁ?" አላቸው። "ንጉሡ ይፈልገዋልና ወጣቱን መነኩሴ ሚሳኤልን" በማለት መለሱለት። እርሱም "ይህን ሽማግሌ ተውት፣ እኔ ወደ እርሱ እመራችኋለሁ" አላቸው። እነርሱም እኔን ደካማውን ይሴሐቅን ከእስራቴ ፈትተው የተባረከውን ቅዱስ አባ ሚሳኤልን ወሰዱት። ከገዳሙ ወጥተው ሐዲዱ፣ እርሱንም በድጋሜ ሳላየው ቀረሁ። እኔ

እና ወንድሞቼ ለብዙ ቀናት መራራ ልቅሶን አለቀስን። ...

ከአንድ ዓመት በኋላ በአገሩ ታላቅ ረሃብ ሆነና ከምግብ እጥረት የተነሣ ብዙ ሕዝብ ሞተ፤ እኔ ግን ቅዱሱ አባት አባ ሚሳኤል አስቀድሞ አስጠንቅቆኝ ስለነበር እጅግ ብዙ ስንዴ፣ በቆሎ፣ አጃና ባቄላ ሰብስቤ በገዳሙ አስቀምጬ ነበር። ይህም የረሃቡን ቀናት በደህና እንድናሳልፍ አደረገን።

አገረ ገዢው በገዳሙ ውስጥ ብዙ እህል እንዳከማቸን በሰማ ጊዜ ምግብ ሊለምነን መጣ። በመጨረሻም ወደ እኛ እየመጣ እህል የሚጠይቀን ሰው እየበዛ ሲመጣ "በረሃቡ ዘመን ወደ አንተ እመጣለሁ" ያለኝን የቅዱሱን ቃል አስታውሼ አለቀስሁ።

አገረ ገዢውና እርሱ የሚያስተዳድረው ሕዝብ በገዳሙ ያከማቸነውን እህል መመገባቸውን ቀጠሉ። አንድ ቀን ድንገት ሰዎች ተሰብስበው ወደ ገዳሙ መጡና አገረ ገዢውን "በዚህ ምድረ በዳ ውስጥ ምን እየሠራህ ነው?" አሉት። አገረ ገዢውም "ምግብ! እነርሱ (መነኮሳቱ) በየትኛውም የምድር ክፍል የማይገኝ ምግብ አላቸው!" በማለት ሲመልስላቸው እነርሱም ወዲያውኑ "በቅጽበት ይህን ገዳም ለቅቀህ ውጣ፤ በሰይፍ እንዳትሞት እንዳትመለስ!" አሉት። አገረ ገዢውና አብሮት የነበረው ሕዝብ በፍጥነት ገዳሙን ለቅቀው ወጡ፤ በገዳሙ ላይም ምንም ዐይነት ጉዳት ሳይደርስ ቀረ።

እኔ ይስሐቅም እነዚህ ሰዎች እነማን እንደሆኑ ለማወቅ ጓጓሁ፤ የሚበሉት ምግብ በሰጠኋቸው ጊዜ "አንበላም፤ ምግብ የሚያስፈልግህ አንተ ነህ" አሉኝ። እኔም ከመካከላቸው ሽምገል ወዳለው ቀረብሁና "ወንድሜ፣ እባክህ ከወዴት እንደሆናችሁ ንገረኝ?" አልሁት። ከዚያም ከአባቶች አንዱ "ንጉሡ ይህን ምድረ በዳ እንድንጠብቅ እና በነዋሪዎች

ላይም ምንም ዐይነት ጉዳት እንዳይደርስ እንድናደርግ ኃላፊነት ሰጥቶናል" አለኝ። እኔም በፊታቸው ከመሬት ላይ ወድቄ እነማን እንደሆኑ እንዲነግሩኝ ለመንኋቸው፤ ግን ቀና ብዬ ስመለከት ከገዳሙ ወጥተው ወደ ምድረ በዳ ሂደዋል፤ ስለዚህም ባየሁትና በሰማሁት ነገር ብዙ አሰብሁ። ...

ዙር ስል አንድ የወጣት ፊት ያለው ሰው ከኋላ ቀርቷል። ይህ ወጣት ወደ እኔ መጣ፤ እጄን ይዞ ከፊት ለፊቴ ተቀመጠና እንዲህ አለኝ፡ - "ተወዳጁ አባቴ ይስሐቅ ሆይ፣ በእውነት እግዚአብሔር ለእኔ ሲበጣ ቸር ሆነልኝ፤ እኔ አንተ የምንኩስና ልብስ ያለበስኸኝ ልጅህ ሚሳኤል ነኝ። ከእኔ ጋር አብረውኝ የነበሩት ሰዎች እኔን ከገዳሙ አስወጥተው ከአንተ ለይተው የወሰዱኝ ሰዎች ናቸው፤ አስቀድሜ እንደነገርሁህ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከገዳሙ መነኮሳት ወንድሞቼ ውስጥ አንዱም እንኳ አላየኝም። አሁን ያየሃቸው ሰዎችም ሰማያዊያን ሠራዊት ናቸው፤ ስለመጡባት ከተማም እስክንድርያ እያሉ የጠሯት ኢየሩሳሌምን ነው። ከእነርሱ ጋር በአንድነት በምድረ በዳው ውስጥ እና አባቶች በፈሪሃ እግዚአብሔር እና በፍጹም መታመን በሚኖሩባቸው በሌሎች ቦታዎች እዞራለሁ።" እኔ ይስሐቅም "ተወዳጁ ወንድሜ ሆይ፣ ሌሎች ብዙ እረኞች አሉና በገዳሙ ውስጥ ካለኝ የእረኝነት ኃላፊነት አርፍ ዘንድ ከአንተ ጋር መሆን እችላለሁ?" ብዬ ጠየቅሁት። እርሱ ግን "አባ፣ ለአንተ በዚህ ገዳም ውስጥ ያሉ ወንድሞችን እንድትጠብቃቸውና በመንፈስ ቅዱስ እንድትመራቸው ከሰማይ ስልጣን ተሰጥቶሃልና ይህ ሊሆን አይችልም፤ ስለዚህ አትፍራ አባ ይስሐቅ" አለኝ። በውብ ቃላቶቹ አጽናናኝ፤ ከዚያም በገዳሙ ስለሚኖሩ ወንድሞቼ ጠየቀኝ። ሰላምታውን ለእያንዳንዳቸው እንዳደርስ ነገረኝ፣ ከዚያም ዋትውልድ ከተማዬ ሊቀ ጳጳስ ወደሆነው ወደ አባ አትናቴዎስ ሒድና መጂቹ ለእኔ ያስቀመጡትን ቀሪ ገንዘብ ውሰድ፤ በስሜም በዚህ ገዳም ውስጥ

ቤተ ክርስቲያን ሥራ" አለኝ። ይህን ካለኝ በኋላ ከእኔ ተለይቶ ወደ ጓደኞቹ ሂዶ ደረሰባቸው። ...

ከዚህ ተአምራዊ ክስተት በኋላ አባ ሚሳኤል እንደጠየቀኝ በቀጥታ ወደ አባቴ ወደ ሊቀ ጳጳስ አባ አትናቴዎስ ሔድኹ። ሊቀ ጳጳስ አባ አትናቴዎስ 1800 ፓውንድ የሚያወጣ ወርቅ፣ 400 ከሱፍ የተሠራ ልብስ፣ 100 የበግ ቆዳ እና 500 ፊረሶች ሰጠኝ። በዚህ ሁሉ ሀብትና ንብረት በጣም ተገረምሁ።

ወደ ገዳም ተመልሼ የአባ ሚሳኤል በአት የነበረችውን ወደ ቤተ ክርስቲያን ለወጥኋት። በአባ ሚሳኤል ስም የታነፀችው ቤተ ክርስቲያን የምትመረቅበት ቀን ደረሰ። እጅግ ብዙ ሕዝብ ከላይኛው ግብፅ ገዳማትና ከተሞች ተሰበሰበ፤ የፋኦው ሊቀ ጳጳስ (Bishop of Fao) ከብዙ ካህናትና መነኰሳት ጋር በዕለቱ ተገኝቶ ነበር። ቅዳሴ ቤቱን ለማክበር ጸሎት ሲጀመር ከአሁን በፊት ያየኋቸውን ሰዎች አሁንም በድጋሜ አየኋቸው። በእጆቻቸው በትር ይዘው ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ገቡ፤ ከበትራቸው የመስቀል ቅርፅ ያለው ብርሃን ይወጣ ነበር። ምንም እንኳን እኔ ከፊቴ ቁመው ባያቸውም ሌላ ማንም አላያቸውም ነበር። እኔም ወደ እነርሱ ተቃረብሁና በፊታቸው ተንበርክኬ እንዲጸልዩልኝ ጠየቅኋቸው። ከዚያም ወደምወደው ልጄ ወደ ሚሳኤል ሔድኹና ሰላምታ አቀረብሁለት።

እነርሱም ሥርዓቱ እስኪፈጸም ድረስና ሁሉም ሰው ወደየመጣበት እስኪሔድ ድረስ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ቆዩ። ከዚያም እነርሱም ተከትለው ወጥተው ሲሔዱ አባ ሚሳኤል ግን ከኋላ ቀረ። ወደ እኔ መጣና "አባ ይስሐቅ፣ በሚቀጥለው ዓመት በዚች ቀን ጌታ ወዳዘጋጀልህ ወደ እግዚአብሔር ቅዱስ ሥፍራ ትሄዳለህና በዚህ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የራስህን መቃብር አዘጋጅ" አለኝ።

ከዚያም አባ ሚሳኤል ሰመጨረሻ ጊዜ ከእኔ ተለይቶ ሔደ፤ እኔም በድጋሜ ሳላየው ቀረሁ። መቃብሬን ከቤተ ክርስቲያኑ በስተሰሜን በኩል እንዲዘጋጅ አደረግሁ።

እኔ ይስሐቅ አባ ሚሳኤልን ከልጅነቱ ጀምሮ አይቸዋለሁ፤ አውቀዋለሁም። እርሱም ሁሉንም ዓለማዊና ሥጋዊ ፍላጎቶች እና ደስታዎች በመናቅ ለእግዚአብሔር ትእዛዛት ታማኝ ሆኖ ኖረ። ባለማቋረጥ በመጸለይና በማመስገን ልክ እንደ እግዚአብሔር መልአክ ነበር።

ቤተ ክርስቲያናችን የአባ ሚሳኤልን የመታሰቢያ በዓል በየዓመቱ ታኅሣሥ 13 ታከብራለች።

በረከቱ ከሁላችን ጋር ይሁን። ክብርና ምስጋና ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለም ለቅድስት ሥላሴ ይሁን። አሜን።

